የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

# በምርጫ ሂደት በየደረጃው ስለሚኖር ቅሬታ አቀራረብ፣ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አደረጃጀት እና አሰራር መመሪያ ቁጥር 10/2013

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ

### አንቀጽ 1. አውጪው ባለስልጣን

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ በምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ስነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2012 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 7፣ 14 ንዑስ አንቀጽ 7፣ 15 ንዑስ አንቀጽ 10 እና 151 ንዑስ አንቀጽ 5 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል። የዚህ መመሪያ ዓላማ የምርጫው ሂደት ነፃ፣ ፍትሀዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ ሆኖ ሳይጓተት እንዲጠናቀቅ ለማስቻል በምርጫው ሂደት የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በህግ አግባብና ግልጽ በሆነ ስርዓት ማስተናገድ ነው።

### አንቀፅ 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ***“የምርጫ ጉዳዮች ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች መመሪያ ቁጥር10/2013”*** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### አንቀፅ 3. ትርጓሜ

1. **“አዋጅ”** ማለት የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ስነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 ነው።
2. **“ኮሚቴ”** ማለት በአዋጁ በተደነገገው መሰረት በየደረጃው የሚቋቋመው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ነው

3. የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በአዋጁ እና በብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ. 1133/2011 ላይ የተሰጡ የቃላትና ሐረጋት ትርጉሞች ለዚህ መመሪያም ተፈፃሚነት አላቸው፡፡

**አንቀፅ 4. የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በመራጮች ምዝገባ፣ በእጩ ምዝገባ፣ በድምፅ አሰጣጥ፣ በድምፅ ቆጠራ እና ሌሎች ከምርጫ ሂደቱ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ምክንያት በሚነሱ ቅሬታዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 5. የፆታ አገላለፅ**

በዚህ መመሪያ ላይ በአንደኛው ፆታ የተደነገገው አነጋገር ለሌላኛው ፆታም ያገለግላል፡፡

**አንቀጽ 6. ዓላማ**

የዚህ መመሪያ ዓላማ የምርጫው ሂደት ነፃ፣ ፍትሀዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ ሆኖ እንዲቀጥልና ያለምንም መጓተት እንዲጠናቀቅ ለማስቻል በምርጫው ሂደት ወቅት የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በህግ አግባብና ግልጽ በሆነ የአሰራር ስርዓት ማስተናገድ ነው፡፡

## ምዕራፍ ሁለት
## የቅሬታ አቀራረብ እና መልስ አሰጣጥ መርሆች

**አንቀፅ 7. የቅሬታ አቀራረብ መርሆች**

ማንኛውም ቅሬታ አቅራቢ ቅሬታውን ሲያቀርብ፡-

ሀ) በቅን ልቦና ላይ ተመስርቶ እና ሆነ ብሎ የምርጫ ሂደቱን ለማደናቀፍ ወይም ለማጓተት ከሚደረጉ ተግባራት በራቀ መልኩ እና፣

ለ) የተፈጸመ የህግ ወይም የአሰራር ግድፈት እንዳለ ባደረበት እምነት ላይ በመመስረት መሆን አለበት።

## አንቀፅ 8. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አሰራር መሰረታዊ መርሆዎች

በየደረጃው ያሉ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች፡-

1. የምርጫው ሂደት ነፃ፣ ፍትሀዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ ሆኖ እንዲቀጥል ለማስቻል የምርጫውን የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በማድረግ ቅሬታዎችን መቀበልና አፋጣኝ ውሳኔ መስጠት፣
2. አፋጣኝ ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮችን ቅድሚያ ሰጥተው ለማየትና ለመወሰን የሚችሉ ቢሆንም ቅሬታ በቀረበላቸው ቅደም ተከተል መሰረትና በህጉ በተሰጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ ውሳኔ መስጠት፣
3. በራሳቸው በኩል አስተርጓሚ ማቅረብ የሚችሉ ከሆነ ይህንን በማድረግ የማይቻል ከሆነ ደግሞ ቅሬታ አቅራቢዎችና መልስ ሰጪዎች የራሳቸውን አስተርጓሚ እንዲያመጡ በመፍቀድ ቅሬታ አቅራቢዎች እና መልስ ሰጭዎች በሚገባቸው ቋንቋ የመደመጥ እና የማዳመጥ እድል መስጠት፤ አስተርጓሚዎች ስራ ከመጀመራቸው በፊት በኮሚቴዎቹ ፊት የትርጉም ስራውን በታማኝነት የሚያከናውኑ ስለመሆኑ ቃለ መሓላ እንዲፈፅሙ ማድረግ፣
4. አሰራራቸውን ለህዝብ ግልፅ ማድረግ፣
5. ለሚሰጡት ውሳኔ አዋጁን፣ አግባብነት ያላቸውን መመሪያዎች እና የቀረበን ማስረጃ መሰረት አድርጎ ውሳኔ መስጠት እና ለውሳኔያቸው በቂ ትንታኔ በፅሁፍ መስጠት እና
6. ለህግ እና ለህሊናቸው ታማኝ በመሆን መስራት አለባቸው፡፡

## አንቀፅ 9. የቦርዱ ስልጣን

1. ቦርዱ በዚህ መመሪያ መሠረት የሚቀርቡለትን፣ የምርጫ ሥነ ምግባር ጥሰቶችን ጨምሮ ሌሎች የምርጫ ሂደቱን አስመልክቶ የሚቀርቡለት ቅሬታዎች ወይም ለሚከሰቱ አለመግባባቶች የፖለቲካ ፓርቲዎች በጋራ መድረካቸው እንዲፈቱት የማበረታታት፣ በራሱ አስተዳደራዊ መፍትሔ የመስጠት፣ ጉድለቶችን የማረምና ለሚቀርቡ ቅሬታዎች ወይም አቤቱታዎች ላይ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን አለው፡፡
2. ቦርዱ የሚቀርቡለትን አቤቱታዎች ወይም ቅሬታዎች በአዋጁና የሚያወጣቸው መመሪያዎች በሚደነግጉት የአሰራር ስነ ስርዓት መሠረት መርምሮ ውሳኔ ይሰጥባቸዋል፡፡
3. ቦርዱ ለሚቀርቡለት አቤቱታዎችና ቅሬታዎች በወቅቱ መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችለው አሠራር በየደረጃው በሚገኙ የምርጫ ጽሕፈት ቤቶች ይዘረጋል።

## ምዕራፍ ሦስት

## <u>የቅሬታ ሰሚ አካላት አደረጃጀት</u>

### አንቀፅ 10. በየደረጃው ስለሚኖሩ ቅሬታ ሰሚ አካላት

1. ቦርዱ በአዋጁ መሰረት፡-

    ሀ) የክልል ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፣

    ለ) የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፣

    ሐ) የምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ እንዲቋቋሙ ያደርጋል።

2. በሁሉም ደረጃዎች የሚቋቋሙ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባል መሆን የሚችል ሰው፡-

    ሀ) እድሜው ከ 21 አመት በላይ የሆነ፣

    ለ) በመልካም ስነ ምግባሩ እና ስብእናው የታወቀ፣

    ሐ) የማታለል ይዘት ያለባቸው ፣ ሆነ ብሎ በሰው አካል ላይ ከባድ ጉዳት የማድረስ እና የምርጫ ነክ ወንጀሎች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ተላልፎባት የማያውቅ፣

    መ) ማንበብ እና መፃፍ የሚችል እና በአካባቢው የስራ ቋንቋ መስራት የሚችል፣

    ሠ) የማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት አባል፣ እጩ ወይም የግል እጩ ወይም የእጩ ወኪል ያልሆነ፣

    ረ) ምርጫው በሚካሄድበት የምርጫ ክልል ነዋሪ የሆነ፣

    ሰ) ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው።

3. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን በየደረጃው የሚያደራጁ የምርጫ አስፈፃሚዎች በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባልነት የሚመረጡት ሰዎች ከላይ በንኡስ አንቀፅ 2 ላይ የተዘረዘሩን መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።

### አንቀፅ 11. የክልል ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አደረጃጀት

1. እያንዳንዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ከቦርዱ ጋር በመተባበር የሚቀርቡለትን ቅሬታዎች ሰምቶ ውሳኔ የሚሰጥ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ያደራጃል።
2. የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት ሦስት ይሆናሉ፤ ከአባላቱም መካከል ቢያንስ አንድ ሴት መኖር አለበት።

3. የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ በመሆን ያገለግላል፡፡
4. የክልል ቅርንጫፍ ፅሕፈት ቤት የእጩዎች ምዝገባ ከመጀመሩ ከ15 ቀናት አስቀድሞ ሰባት እድሜያቸው 21 እና ከዚያ በላይ የሆነ ሰዎችን መርጦ ለህዝብ አስተያየት በፅ/ቤቱ ግቢ ውስጥ በመለጠፍ እና በሌላ ለህዝብ ግልፅ በሆነ መንገድ ለተከታታይ ሶስት ቀናት ግልጽ በማድረግ ህዝብ አስተያየት እንዲሰጥባቸው ካደረገ በኋላ ተቀባይነት ያለው ቅሬታ ያልቀረበባቸው መሆኑን በማረጋገጥ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (5) መሠረት ይመርጣቸዋል፡፡
5. ከላይ በንኡስ አንቀፅ (4) ከቀረቡ እና ምክንያታዊ የሆነ ቅሬታ ያልቀረበባቸውን ሰዎች ዝርዝር ውስጥ የመጀመሪያ ሁለቱን የኮሚቴው አባላት እንዲሆኑ በማድረግ በሶስተኛ፣ በአራተኛ እና በአምስተኛ ደረጃ ላይ ያሉትን ደግሞ የጎደለ አባል መተካት በሚያስፈልግበት ጊዜ የሚጠሩ ተጠባባቂዎች አድርጎ ይመዘግባል፡፡

## አንቀፅ 12. የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አደረጃጀት

የምርጫ ክልሉ ፅ/ቤት፡-

1. በእያንዳንዱ የምርጫ ክልል የምርጫ ክልል አስፈፃሚ አባላትን ሳይጨምር በምርጫ ክልሉ በመራጭነት ለመመዝገብ ብቁ ከሆኑ ነዋሪዎችና በነሱ ጥቆማ ሦስት አባላት ያሉት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ያደራጃል፡፡
2. አንድ የምርጫ ክልሉ የምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ያለድምፅ የሚሳተፍ የኮሚቴው አባል ሲሆን ከአባላቱ መካከል ቢያንስ አንድ ሴት መኖር አለባት፡፡
3. ከተጠቆሙት ሰዎች መሃል አንዷ ብቻ ሴት ከሆነች በቀጥታ ውድድር ውስጥ ሳትገባ ከላይ በአንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 2 የተዘረዘሩ መስፈርቶችን ማሟላቷን በማረጋገጥ የኮሚቴው አባል እንድትሆን ይደረጋል፡፡
4. የምርጫ ክልሉ አስፈፃሚዎች ሰብሳቢ ወይም ሰብሳቢው የወከለው የምርጫ አስፈፃሚ የማስመረጥ ሂደቱን በሚከተለው መልኩ እንዲከናወን ያደርጋል፡-

    ሀ) የምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት በተቋቋመ በሁለት ቀናት ጊዜ ውስጥ ለምርጫ ክልሉ ነዋሪዎች የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላቱን እንዲመርጡ ጥሪ የሚያደርግ በምርጫ ክልሉ

ፅ/ቤት አካባቢ ለማስታወቂያ መለጠፊያ ምቹና በቀላሉ ተደራሽ ሊሆኑ በሚችሉ ቦታዎች ሁሉ ለህዝብ ግልፅ በሆነ ቦታ ላይ ማስታወቂያ ይለጥፋል፣

ለ) ማስታወቂያው የምርጫ ክልሉ ነዋሪዎች ማስታወቂያው በተለጠፈ በአራተኛው ቀን በግልፅ በተቀመጠ ሰአት እና ቦታ እንዲሰበሰቡ ጥሪ የሚያደርግ ይሆናል፣

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4(ለ) ስር እንደተደነገገው ማስታወቂያው በተለጠፈ በአራተኛው ቀን በማስታወቂያው መሰረት በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት ምርጫ ላይ ለመሳተፍ የመጡትን ሰዎች ይሰበስባል፣

መ) የተሰበሰቡት ሰዎች ከምርጫ ክልሉ ነዋሪዎች መካከል ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባልነት ይሆናሉ የሚሏቸውን ከላይ በአንቀፅ 10 ንኡስ አንቀፅ (2) ላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ሰባት ሰዎች ይጠቁማሉ፤ በእጩነት የሚጠቆመው በስብሰባው ላይ የተገኘ ሰው ብቻ ነው፣

ሠ) የምርጫ ክልሉ ሰብሳቢ ወይም ሂደቱን እንዲያስፈፅም የወከለው ምርጫ አስፈፃሚ የተጠቆሙት ሰዎች ከላይ በአንቀፅ 10 ንኡስ አንቀፅ (2) ላይ የተዘረዘሩ መስፈርቶችን የሚያሟሉ መሆኑን እና ፍቃደኝነታቸውን ጠይቆ ያረጋግጣል፣

ረ) ከተጠቆሙት ሰባት ሰዎች መካከል ባገኙት ድምፅ ከአንደኛ እስከ አምስተኛ የሆኑትን ስም ዝርዝር በመያዝ የመጀመሪያ ሶስቱ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት እንዲሆኑ በማድረግ ሌሎች ከአራተኛ እስከ ሰባተኛ ደረጃ ያሉት በተጠባባቂነት የጎደለ አባል ሲኖር የሚያሟሉ እንዲሆኑ ይደረጋል፣

ሰ) ይህንን ምርጫ እንዲያከናውን የተመደበው የምርጫ ክልሉ ምርጫ አስፈፃሚ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት አመራረጥ ሂደቱ በቃለ ጉባኤ መያዙን ያረጋግጣል። የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላቱን ምርጫ ለመታዘብ የመጡ እውቅና የተሰጣቸው ታዛቢዎች የተገኙ እንደሆነ ታዛቢዎቹ በቃለ ጉባኤው ላይ መፈረማቸውን ያረጋግጣል።

5. ከላይ በተቀመጠው መሰረት የተመረጡት ሶስት የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላትና በአዋጁ አንቀፅ 13 ንዑስ ቁጥር 6 ላይ እንደተመለከተው ያለድምፅ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው አባል በመሆን በሚሳተፈው የምርጫ አስፈፃሚ ሰብሳቢነት ስራቸውን የሚያከናውኑ ይሆናል።

## አንቀፅ 13. የምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አደረጃጀት

የምርጫ ጣቢያ ምርጫ አስፈጻሚ፡-

1. በምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በሚመደብ የምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ሰብሳቢነት የሚመራ ሦስት አባላት የያዘ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ያደራጃል:: ከኮሚቴ አባላት ቢያንስ አንዷ ሴት መሆን አለባት፡፡
2. ከተጠቆሙት ሰዎች መሃል አንዷ ብቻ ሴት ከሆነች በቀጥታ ውድድር ውስጥ ሳትገባ ከላይ በአንጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 2 የተዘረዘሩ መስፈርቶችን ማሟላቷን በማረጋገጥ የኮሚቴው አባል እንድትሆን ይደረጋል፡፡
3. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ከምርጫ ጣቢያው የምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ውስጥ የሚመድበው ሰው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ በመሆን ይሠራል፡፡
4. ሌሎች ሁለት የምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት በጣቢያው ለምርጫ ከተመዘገቡ መራጮች መካከል በሚከተለው ስርአት ይመረጣሉ፡-

    ሀ) የመራጮች ምዝገባ በተጀመረ በሁለተኛው ቀን በግልፅ በተቀመጠ ሰአት እና ቦታ የምርጫ ጣቢያ ነዋሪዎች እንዲሰበሰቡ ጥሪ የሚያደርግ ማስታወቂያ በምርጫ ጣቢያው ፅ/ቤት በር ላይ እና በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ለህዝብ ግልፅና ተደራሽ በሆነ ቦታ ይለጠፋል፡፡

    ለ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4(ሀ) ስር እንደተደነገገው ማስታወቂያው በተለጠፈ በሁለተኛው ቀን በኮሚቴው አባላት ምርጫ ላይ ለመሳተፍ የመጡትን ሰዎች ይሰበስባል፣

    ሐ) የተሰበሰቡት ሰዎች ከምርጫ ጣቢያው የተመዘገቡ መራጮች መካከል ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት ይሆናሉ የሚሏቸውን ከላይ በአንቀፅ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟሉ 7 ሰዎችን እጅ በማውጣት ይጠቁማሉ፣

    መ) የምርጫ ጣቢያው ሰብሳቢ የተጠቆሙት ሰዎች በኮሚቴ አባልነት ለመስራት ያላቸው ፍቃደኝነት እና ከላይ በአንቀፅ 10 ንኡ አንቀጽ 2 ላይ የተዘረዘሩ መስፈርቶችን የሚያሟሉ መሆኑን ጠይቆ ያረጋግጣል፣

    ሠ) ከተጠቆሙት 7 ሰዎች መካካል በእጅ ማውጣት በተከናወነው ድምፅ አሰጣጥ ባገኙት ድምፅ ከአንደኛ እስከ አምስተኛ የሆኑትን ስም ዝርዝር በመያዝ የመጀመሪያ ሁለቱን የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት እንዲሆኑ በማድረግ ሌሎች ከሶስተኛ እስከ አምስተኛ ደረጃ ያሉትን በተጠባባቂነት በመያዝ የጎደለ አባል ሲኖር የሚያሟሉ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

## አንቀፅ 14. ከቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባልነት ስለመነሳት

1. ማንኛውም የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባል ከታች በተዘረዘሩት ማናቸውም ምክንያቶች የተነሳ ለኮሚቴው የቀረበውን ጉዳይ ማየት የለብኝም ብሎ ካመነ ለሚመለከተው የክልል ቅርንጫፍ፣ የምርጫ ክልል ወይም ምርጫ ጣቢያ ኃላፊ በጽሁፍ በማስታወቅ እራሱን ያገላል፡-

    ሀ) ለኮሚቴው የቀረበን ቅሬታ ቀደም ሲል በሥራው ምክንያት ያየው ከሆነ፣

    ለ) እራሱን፣ አባቱን፣ እናቱን፣ አያቱን፣ ልጁን፣ እህቱን፣ ወንድሙን፣ አክስቱን፣ አጎቱን ወይም የትዳር አጋሩን፣ የትዳር አጋሩን ወንድም፣ እህት፣ እናትና አባት የሚመለከት ጉዳይ ከሆነ ወይም

    ሐ) በማናቸውም ሌላ ሁኔታ ጉዳዩን በገለልተኝነት ለማየት የማያስችለው መሆኑን ሲረዳ።

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ስር ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ውስጥ አንዱ አለ ብሎ የሚያምን ቅሬታ አቅራቢ ወይም ተጠሪ ጉዳዩ የሚመለከተው የኮሚቴ አባል ይነሳልኝ ብሎ ማመልከት ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሠረት አንድ የኮሚቴ አባል ከቀረበው ጉዳይ ልነሳ የሚል ማመልከቻ ሲያቀርብ ጥያቄው የቀረበለት የምርጫ ጣቢያ፣ የምርጫ ክልል ወይም የክልል ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ኃላፊ የቀረበውን የልነሳ ጥያቄ ወዲያውኑ ተቀብሎ የቀረበው ቅሬታ ቀደም ሲል ለኮሚቴ አባልነት በተጠባባቂነት ከተያዙት ሰዎች መካከል አንዱን፣ ከተጠባባቂዎቹ አንድም ሰው ያልተገኘ ከሆነ ደግሞ ከምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት አንዱን ወዲያውኑ በመተካት እንዲታይ ያደርጋል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት አንድ የኮሚቴ አባል ይነሳልኝ የሚል ማመልከቻ የቀረበለት ከክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት፣ የምርጫ ክልል ወይም የምርጫ ጣቢያ ኃላፊ ማመልከቻውን ከቀረበው ማስረጃ ጋር በማገናዘብ ቅሬታው ተቀባይነት አለው ወይም የለውም የሚል ውሳኔ ወዲያውኑ ይሰጣል። የቀረበው የይነሳልኝ ጥያቄ ተቀባይነት ያገኘ ከሆነ ለኮሚቴው የቀረበው ቅሬታ ቀደም ሲል ለኮሚቴ አባልነት በተጠባባቂነት ከተያዙት ሰዎች መካከል አንዱን፣ ከተጠባባቂዎቹ አንድም ሰው ያልተገኘ ከሆነ ደግሞ ከምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት አንዱን ወዲያውኑ በመተካት እንዲታይ ያደርጋል፡፡

5. ከላይ በተመለከቱት የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሰረት የኮሚቴ አባል ከአባልነት መገለል ወይም መነሳት የተከሰተው በክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ከሆነ የተነሳውን የኮሚቴ አባል ለመተካት ከተጠባባቂዎቹ አንድም ሰው ያልተገኘ ከሆነ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን አንድ ሰራተኛ በመተካት ለኮሚቴው የቀረበው ጉዳይ እንዲታይ ይደረጋል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሰረት የኮሚቴ አባል እራስን ማግለል ወይም መነሳት ውሳኔ ተፈፃሚ የሚሆነው ጥያቄ በቀረበበት ቅሬታ ጉዳይ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም የኮሚቴው አባል በሌሎች ጉዳዮች ላይ መደበኛ ሥራውን ይቀጥላል፡፡

## አንቀፅ 15. የተጓደሉ ቅሬታ ሰሚ አባላትን ስለመተካት

1. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት በተለያየ ምክንያት ሲጓደሉ ወዲያውኑ መተካት አለባቸው፣
2. በየደረጃው ያሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት ሲጓደሉ ለየደረጃው በተጠባባቂነት ከተመዘገቡ ሰዎች መካከል እንደየቅደም ተከተላቸው ተክተው እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

## <u>ምዕራፍ አራት</u>

## <u>የቅሬታ አቀራረብ እና አፈታት ሥርዓት</u>

## አንቀፅ 16. በመራጮች ምዝገባ ስለሚነሱ ቅሬታዎች እና አፈታታቸው

1. ማንኛውም ሰው በመራጭነት ከመመዝገብ የተከለከለ እንደሆነ ለምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡
2. በመራጭነት መመዝገብ የሌለበት ሰው ያለአግባብ ተመዝግቧል የሚል ተቃውሞ ያለው ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት ተቃውሞውን ለምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሰረት የሚቀርብ ቅሬታ የማቅረቢያ ጊዜ ከመራጮች የምዝገባ ቀን ጀምሮ የመራጮች መዝገብ ለህዝብ ይፋ የሚሆንበት ጊዜ እስከሚያልቅ ድረስ ነው፡፡ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 መሰረት የምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ከመቋቋሙ በፊት የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ተቀብሎ በማስቀመጥ ኮሚቴው እንደተቋቋመ ወዲያውኑ የቀረቡትን ማመልከቻዎች ለኮሚቴው ያስረክባል፡፡

4. የምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ከላይ በንዑስ አንቀፅ (1) ወይም (2) ለቀረበለት ቅሬታ በአምስት ቀናት ውስጥ ውሣኔ መስጠት አለበት። የምርጫ ጣቢያው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ጉዳዩ በቀረበለት በአምስት ቀናት ውስጥ ምላሽ ካልሰጠ ወይም ቅሬታ አቅራቢው በተሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ እንደሆነ ውሳኔው በተሰጠው ወይም የአምስት ቀን ጊዜ ገደቡ እንዳለፈ በአምስት ቀናት ውስጥ ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል።
5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4) መሠረት ቅሬታ የቀረበለት የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ለቀረበለት ቅሬታ በአምስት ቀናት ውስጥ ውሣኔ መስጠት አለበት።
6. የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በአምሰት ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ወይም ቅሬታ አቅራቢው በተሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ እንደሆነ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በአምስት ቀናት ውስጥ አካባቢያዊ ስልጣን ባለው የፌደራል ወይም የክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩ እንዲታይለት ቅሬታ የማቅረብ መብት አለው። ቅሬታ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የቀረበለትን ቅሬታ ለመወሰን የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን አስቀርቦ በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል።
7. የምርጫ ጣቢያው የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ሥራውን ያከናውናል። ነገር ግን የምርጫ ክልሉን ውሳኔ የሚሽር የፍርድቤት ውሳኔ የደረሰው እንደሆነ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ ተግባራዊ ማድረግ አለበት።

### አንቀፅ 17. በእጩዎች ምዝገባ ሂደት ስለሚነሱ ቅሬታዎች

1. ማንኛውም ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት በእጩነት ከመመዝገብ የተከለከለ እንደሆነ ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው።
2. አንድ በእጩነት የተመዘገበ ሰው በእጩነት መቅረብ የለበትም የሚል ተቃውሞ ያለው ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሰረት የሚቀርብ ቅሬታ የማቅረቢያ ጊዜ ከእጩዎች ምዝገባ ቀን ጀምሮ የተመዘገቡ እጩዎች ጊዜያዊ ዝርዝር ይፋ ከሆነበት ቀን ቀጥሎ ባሉት ሁለት ቀናት ውስጥ ይሆናል።
4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ (1) ወይም (2) መሰረት ቅሬታ የቀረበለት የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን ቅሬታ መርምሮ በአምስት ቀናት ውስጥ ውሣኔ ይሰጣል።

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሰረት በምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በተሰጠ ውሳኔ ቅር የተሰኘ የፖለቲካ ድርጅት እጩ ወይም የግል እጩ በምርጫ ክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ለሚቋቋም ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በሰባት ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡
6. ከላይ በንኡስ አንቀፅ (5) መሰረት ቅሬታ የቀረበለት የክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን በመመርመር በሰባት ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በጽሑፍ ይሰጣል፡፡ የምርጫ ክልሉም የክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት ስራውን ያከናውናል፡፡
7. የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በሰባት ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ወይም ቅሬታ አቅራቢው በተሰጠው ውሳኔ ካልተስማማ እንደአግባቡ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወይም ቅሬታው የተነሳው በአዲስ አበባ ወይም ድሬደዋ ውስጥ ከሆነ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቅሬታ የማቅረብ መብት አለው፡፡ ፍርድ ቤቱም የቀረበለትን ቅሬታ ለመወሰን የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን አስቀርቦ በመመርመር በ15 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
8. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የክልል ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የሰጠውን ውሳኔ የሚቀይር ውሳኔ የሰጠ እንደሆነ የምርጫ ክልሉ ፅ/ቤት በፍርድ ቤቱ ውሳኔ መሰረት ስራውን ያከናውናል፡፡

## አንቀፅ 18. በድምፅ አሰጣጥ ሂደት ስለሚነሱ ቅሬታዎች

1. አንድ የተመዘገበ መራጭ ድምፅ ከመስጠት ሲከለከል ቅሬታውን ወዲያውኑ ለምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በማቅረብ የድምፅ መስጠት ሂደቱ ከመጠናቀቁ በፊት ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡ ቅሬታው ድምጽ ከመስጠት በተከለከለው እጩ ወይም በወኪሉ ሊቀርብ ይችላል፡፡
2. ቅሬታ የቀረበለት የምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴም ጉዳዩን በማጣራት፡-

   ሀ) መራጩ ድምፅ የመስጠት መብት እንዳለው በመወሰን ድምጹን እንዲሰጥ ሊወስን ወይም

   ለ) ቅሬታ አቅራቢው ለዚሁ በተዘጋጀው ፖስታ ጊዜያዊ ድምፅ እንዲሰጥ በማድረግ ቅሬታ አቅራቢው ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አመልክቶ የተሰጠው ድምጽ ትክክለኛ ድምጽ ነው ተብሎ እንዲወሰንለት እንዲጠይቅ ይገልጽለታል ወይም

ሐ) ድምጽ ከመስጠት የተከለከለ ሰው በማያጠራጥር ሁኔታ ድምጽ የመስጠት መብት የሌለው ሰው ነው ብሎ ካመነ የቀረበውን ቅሬታ ውድቅ በማድረግ አመልካቹ ድምጽ እንዳይሰጥ ይወስናል።

3. በምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ቅር የተሰኘ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ለ) በተመለከተው መሰረት ጊዜያዊ ድምጽ የሰጠ መራጭ ወዲያውኑ ቅሬታውን ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም ለወረዳ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል። ፍርድ ቤቱም የድምጽ ማዳመሩ ሂደት ውሳኔውን እስኪሰጥ ድረስ እንዲዘገይ ሊያዝ ይችላል፤ በቀረበው ቅሬታ መሰረት ፍርድ ቤቱ ቅሬታ አቅራቢው የመምረጥ መብት አለው ብሎ ከወሰነ የተሰጠው ጊዜያዊ ድምጽ ተቀባይነት ያገኛል።
4. ቅሬታ አቅራቢው በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 መሰረት የተወሰነውን ውሳኔ ለሚመለከተው ለምርጫ ክልል ጽ/ቤት ማስረከብ ይኖርበታል።
5. ከላይ በንዑስ አንቀፅ (2)(ለ) መሠረት ጊዜያዊ ድምፅ የሰጠው ቅሬታ አቅራቢ በምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ወይም በፍርድ ቤት ጊዜያዊ ድምጹ እንዲፀናለት ከተወሰነለት እና እራሱ ወይም ህጋዊ ወኪሉ የድምፅ ማዳመሩ ሰዓት ከመጠናቀቁ በፊት ለምርጫ ጣቢያው ውሳኔውን ካላቀረበ የሰጠው ጊዜያዊ ድምፅ ሳይቆጠር ውድቅ ይደረጋል።
6. አንድን መራጭ ድምፅ መስጠት የለበትም የሚል ተቃውሞ ያለው ሰው ቅሬታ አቀራረብ እና ውሳኔ አሰጣጥ ከላይ ድምፅ እንዳልሰጥ ተከለከልኩ የሚል ቅሬታ የሚታይበት አሰራር በተደነገገው መሠረት ቅሬታውን በየደረጃው በፅሑፍ የማቅረብና ውሣኔ የማግኘት መብት አለው። የአንድን ሰው ድምፅ የመስጠት መብት የሚቃወም የእጩ ወኪል ቅሬታውን በየደረጃው አስቀርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው።
7. ከላይ በንኡስ አንቀፅ (6) የተመለከተው ቅሬታ የቀረበለት የምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ጉዳዩን በማጣራት፡-

    ሀ) የቀረበውን ቅሬታ ውድቅ በማድረግ ቅሬታ የቀረበበት ሰው ድምጽ እንዲሰጥ ሊወስን ይችላል ወይም

    ለ) ያቀረበው ቅሬታ መጣራት ያለበት ሆኖ የታየው እንደሆነ ቅሬታ የቀረበበት ሰው ጊዜያዊ ድምፅ እንዲሰጥ እና ድምፁ ለብቻ በፖስታ እንዲታሸግ በማዘዝ ቅሬታ አቅራቢው ቅሬታ

የቀረበበት ሰው መምረጥ የለበትም ለማለት ያስቻለውን ማስረጃ ጉዳዩን አይቶ ለሚወስነው የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ሐ ) እንደሁኔታው ከምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ወይም አግባብነት ካለው የፌደራል ወይም የክልል ፍርድቤት ቅሬታ የቀረበበት ሰው ድምፅ የመስጠት መብት የለውም የሚል ውሳኔ የድምፅ ማዳመሩ ከመጠናቀቁ በፊት ካላመጣ የተሰጠው ጊዚያዊ ድምፅ እንዲቆጠር ይደረጋል፡፡

መ) ድምጽ እንዳይሰጥ ቅሬታ የቀረበበት ሰው በማያጠራጥር ሁኔታ ድምጽ የመስጠት መብት የሌለው ሰው ነው ብሎ ካመነ የቀረበውን ቅሬታ በመቀበል አመልካቹ ድምጽ እንዳይሰጥ ይወስናል፡፡

## አንቀፅ 19. በቆጠራ ሂደትና በውጤት ላይ ስለሚነሱ ቅሬታ ዎችና አፈታታቸው

1. በድምፅ ቆጠራ ሂደትና በውጤቱ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም የፓለቲካ ድርጅት ወይም የግል እጩ ወይም ወኪል ቅሬታውን ለምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ወዲያውኑ በማቅረብ ሊያስወስን ይችላል፡፡ የምርጫ ጣቢያው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን ቅሬታ በማየት ወዲያውኑ ወይም ቢዘገይ ቅሬታውን በተቀበለ በ12 ሰዓት ውስጥ ውሳኔውን በፅሁፍ መስጠት አለበት፡፡
2. በኮሚቴው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ቅሬታውን የምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሁለት ቀናት ውስጥ ለምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን ቅሬታ መርምሮ ቅሬታውን ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በሁለት ቀናት ውስጥ በቀረበለት ቅሬታ ላይ ውሳኔ በጽሑፍ ይሰጣል፡፡
3. ከላይ በንኡስ አንቀፅ (1) እና (2) ላይ የተደነገገው ቢኖርም ቅሬታ የቀረበው በምርጫ ክልሉ በተደረገው የድምፅ ማዳመር እና ውጤት ሂደት ላይ ከሆነ ቅሬታ አቅራቢው ቅሬታውን በሁለት ቀን ውስጥ ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብ አለበት፡፡ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴውም ውሳኔውን ቅሬታው በደረሰው በ12 ሰዓት ውስጥ ይሰጣል።
4. ከላይ በንኡስ አንቀፅ (3) መሠረት የቀረበ ቅሬታ ላይ በተሰጠ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ቅሬታውን እንደሁኔታው ለቦርዱ ወይም ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ከታች በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ (5) እና (9) ላይ በተደነገገው መሰረት አቅርቦ ውሳኔ ማግኘት ይችላል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የምርጫ ክልሉ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ቅሬታ አቅራቢ ውሳኔ በተሰጠው በአምሰት ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል፡ ፡ ቦርዱ የቀረበውን ቅሬታ መርምሮ በ10 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
6. ከላይ በንዑስ አንቀፅ (2) እና (4) መሠረት ቅሬታ የሚያቀርብ ማንኛውም የምርጫ አስፈፃሚ፣ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል ዕጩ ወይም ወኪል፤ ለምርጫ ጣቢያ ወይም ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ያቀረበውን ቅሬታ እና የተሰጠውን ውሳኔ ከሚያቀርበው ቅሬታ ጋር ማያያዝ አለበት፡፡
7. የምርጫ ጣቢያው ወይም የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ፦

   ሀ) ውሳኔ እስኪሰጥ ወይም ማጣራት እስኪደረግ ድረስ ቆጠራው እንዲቋረጥ፣

   ለ) ቅሬታ የቀረበበት ቆጠራ እንደገና እንዲካሄድ፤

   ሐ) ቅሬታ የቀረበበት ቆጠራ ትክክል ስለሆነ ቅሬታው አግባብነት የለውም በማለት፤

   መ) የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በቆጠራ ላይ የቀረበው ቅሬታ የምርጫ ጣቢያውን ወይም የምርጫ ክልሉን አጠቃላይ ውጤት በመሠረቱ የማይለውጠው ከሆነ ድጋሚ ቆጠራ ማካሄድ አያስፈልግም በማለት ሊወስን ይችላል፡፡

8. ቦርዱ በቅሬታ መልክ የቀረበለትን የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ሊያጸናው፣ ሊሽረው ወይም ሊያሻሽለው ይችላል፡፡ በተጨማሪም ቦርዱ የሕግ ጥሰት የተከሰተ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 148 መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ እንዲሁም እንደ ጉዳዩ ክብደት ጉዳዩን ለሚመለከተው የህግ አስከባሪ አካል ሊመራው ይችላል፡፡
9. ቅሬታ አቅራቢው ቦርዱ የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ውሳኔ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በአስር ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቅሬታ ማቅረብ ይችላል።
10. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ከላይ በንዑስ አንቀፅ 9 መሠረት ለቀረበለት ቅሬታ ይግባኙ በደረሰው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
11. በሕግ ከተሰጣቸው ሌሎች ስልጣኖች በተጨማሪ ቦርዱ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደ ቅደም ተከተላቸው በአዋጅ ቁ. 1133/2011 አንቀጽ 7 ንኡሰ አንቀጽ 20 እና አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 4 እና በአዋጁ አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 1(ሀ) እንዲሁም ቦርዱ የድጋሚ ምርጫ አተገባበርን በሚመለከት ባወጣው መመሪያ መሰረት ዳግም ምርጫ እንዲካሄድ ሊያዙ ይችላሉ፡፡

12. የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፣ ቦርዱ ወይም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቅሬታ የቀረበበትን የምርጫ ክልል ወይም ክልሎች ውጤት እንዳይገለጽ ሊያዝ ይችላል።

## አንቀፅ 20. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት ተግባርና እና ኃላፊነት

1. በየደረጃው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባል ሆነው ከተመደቡ ሰዎች አንደኛው አባል በተደራቢነት በቃለ ጉባኤ ያዥነት በኮሚቴው ሰብሳቢ ተመድቦ የኮሚቴውን ቃለ ጉባኤዎች እና ውሳኔዎች በጽሁፍ ይይዛል።
2. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት በቅሬታ የቀረበላቸውን ጉዳይ በመመርመር አፋጣኝ እና ህጋዊ ውሳኔ በፅሁፍ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው።
3. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት በዚህ መመሪያ፣ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው መመሪያዎች በአዋጁ ላይ የተቀመጡ መርሆችን መሠረት በማድረግ ውሳኔ መስጠት አለባቸው።

## አንቀፅ 21. የምርጫ አስፈፃሚዎች ኃላፊነት

በየደረጃው የሚገኙ የምርጫ አስፈጻሚዎች፡-

ሀ) የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ እና ፍርድ ቤቶች የሚሰጡትን ውሳኔ ተፈፃሚ ያደርጋሉ፣

ለ) ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት ሥራ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ማስረጃዎችንና ግብአቶችን ያቀርባሉ፣

ሐ) በየደረጃው ያለው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የውይይቶች እና ውሳኔዎች በቃለ ጉባዔ መያዛቸውንና አስፈላጊ ሲሆን ለሚመለከተው አካል መላካቸውን ያረጋግጣል፣

መ) ማናቸውንም ሰነዶች በአግባቡ እንዲጠበቁ ያደርጋሉ፣

ሠ) ቅሬታ የማቅረብ መብት ላለው ሰው የተሟላ ሰነድ በመስጠት ቀጥሎ ላለ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታ የማቅረብ መብቱን እንዲጠቀም ያደርጋሉ።

## ምዕራፍ አምስት

## ስለቅሬታ አቅራቢ፣ ቅሬታ አቀራረብ እና ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ኣሠራር

### አንቀፅ 22. ቅሬታ ማቅረብ ስለመቻሉ

1. ማንኛውም በዚህ መመሪያ መሰረት ቅሬታ የሚያቀርብ ሰው ቅሬታውን በሚያቀርብበት ወቅት ኢትዮጵያዊ መሆኑን የሚገልፅ የማንነት መታወቂያ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ማስረጃ አያይዞ ማቅረብ አለበት።
2. ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ቅሬታውን የሚቀበሉት ቅሬታ አቅራቢው በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ መሰረት በመራጭነት ለመመዝገብ የሚችል ሰው መሆኑን በማጣራት ወይም የምዝገባ ካርዱን በመጠየቅ ካረጋገጡ በኋላ ይሆናል።

### አንቀፅ 23. የቅሬታ አቀራረብ

1. እያንዳንዱ ቅሬታ አቅራቢ የሚያቀርበው ቅሬታ በፅሁፍ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት በሚያስችል መልኩ ግልፅ ሆኖ ተዘጋጅቶ፦

    ሀ) ቅሬታው የተፃፈበት ቀን እና ሰዓት፣

    ለ) የቅሬታ አቅራቢውን ሙሉ ስም፣ ሞባይል ስልክ ቁጥር፣ የኢ-ሜይል አድራሻና አድራሻ፣

    ሐ) ለቅሬታ መነሻ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ፣

    መ) እየተጠየቀ ያለውን መፍትሄ፣

    ሠ) የማስረጃ ዝርዝር፣ የሚቀርበው የሰው ማስረጃ በሆነ ጊዜ የምስክሮቹን ማንነት እና አድራሻ ዝርዝር እና፣

    ረ) ቅሬታው የሚቀርብበት አካል ወይም ሰው ስም እና የሚታወቅ ከሆነ አድራሻ በግልፅ ያመላከተ መሆን አለበት።

    ሰ) ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የሚቀርብ ቅሬታ ቦርዱ ለዚሁ ተግባር ባዘጋጀው ቅፅ በሁለት ቅጂ ተዘጋጅቶ በቅሬታ አቅራቢው በመፈረም ሊቀርብ ይችላል። ሆኖም ቅሬታ አቅራቢው በቦርዱ

በተዘጋጀው ቅጽ ላይ ሞልቶ ቅሬታውን ያላቀረበበትን በቂ ምክንያት ካቀረበ ቅሬታው ውድቅ ሊደረግበት አይገባም።

ሸ) ማንኛውም ቅሬታ በአቤት ባዩ ወይም በሕጋዊ ወኪሉ መቅረብ አለበት፡፡

2. ቅሬታ አቅራቢው የማያነብ ወይም የማይፅፍ ከሆነ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ቅሬ ው በቃል እንዲቀርብ በማድረግ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው አባላት በተገኙበት፡-

ሀ) የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው የቅሬታ አቅራቢውን ቃል ሰምቶ በጽሁፍ ቅፁ ላይ ይመዘግባል፡፡

ለ) የቅሬታ አቅራቢውን ቃል ከላይ በዚህ ንዑስ አንቀፅ (ሀ) መሠረት ሲመዘግብ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገውን መስፈርት ያሟላ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

ሐ) ከላይ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (ሀ) መሠረት ወደ ጽሑፍ የተለወጠው ቅሬታ ለቅሬታ አቅራቢው ተነቦለት በፅሁፍ ወይም በጣት አሻራ ወይም ጣት የሌለው ከሆነ በሚችለው ሌላ ምልክት እንዲፈርምበት ያደረጋል፡፡ በማንኛውም ሁኔታ መፈረም የማይችል ከሆነ የኮሚቴው ሰብሳቢ ይህንኑ ገልፆ ራሱ ይፈርምበታል፡፡

3. ማንኛውም ቅሬታ ለሚመለከተው አካል ከቀረበ በኋላ ቅሬታ አቅራቢው ወይም ህጋዊ ወኪሉ ጉዳዩን እንደማይቀጥልበት ወይም እንዳቋረጠ በፅሁፍ ከገለፀ ቅሬታ ሰሚው አካል ይህንኑ ፅሁፍ ከቅሬታው ጋር በማያያዝ በአጭር ቃለ ጉባኤ ጉዳዩን ይዘጋል፡፡

**አንቀፅ 24. ቅሬታ ስለመቅረቡ የሚሰጥ ማስረጃ**

በየደረጃው ያለ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በማንኛውም ሰው ወይም አካል ቅሬታ ሲቀርብለት በዚህ መመሪያ አንቀፅ 22 እና 23 ያሉትን ዝርዝር ሁኔታዎች ያሟላ መሆኑን በማረጋገጥ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የቀረበው ቅሬታ ቅጂ ላይ ቀንና ሰዓቱን መዝግቦበት በመፈረም ለአቅራቢው ይሰጠዋል፡፡

**አንቀፅ 25. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ስብሰባና ውሳኔ አሠጣጥ**

በየደረጃው የሚቋቋም የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ስብሰባ የሚካሄደው በሙሉ አባላት በተገኙበት ነው። የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቅሬታ አቅራቢውን ቅሬታ፣ ማስረጃ እና ቅሬታ የቀረበበትን አካል ወይም የምርጫ

አስፈፃሚውን ክፍል ምክንያትና መልስ ከሰማ እና የቀረበለትን ማስረጃ ካገናዘበ በኋላ ውሳኔ በጽሁፍ ይሰጣል፡፡

1. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንጽ 4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቅሬታ አቅራቢውም ሆነ ቅሬታ የቀረበበት ሰው በኮሚቴው የመሰማት፣ ማስረጃውን የማሰማትና የመከራከር መብት አለው፡፡
2. ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን ቅሬታ ከመረመረ በኋላ በድምፅ ብልጫ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
3. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ቅሬታ የቀረበበት የምርጫ አስፈፃሚ ወይም አካል መልስ መስጠት ሳያስፈልገው ውሳኔ መስጠት እንደሚቻል ሲያምን ወይም ጉዳዩ ደርሶት መልስ ሳይሰጥ ሲቀር የቅሬታ አቅራቢውን ቅሬታና ማስረጃ በመመርመር ብቻ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡
4. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የሚሰጠው ውሳኔ በበቂ ማስረጃ ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡
5. የሀሳብ ልዩነት ያለው የኮሚቴ አባል ልዩነቱ በአጭሩ እንዲመዘገብለት ሊያደርግ ይችላል፡፡
6. ማንኛውም ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የውይይት ቃለ ጉባኤውን ወይም የሚሰጠውን ውሳኔ በጋራ ፊርማ ማረጋገጥ አለበት፡፡
7. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ የሚከተሉትን አካቶ የያዘ መሆን ይኖርበታል፤

   ሀ) ቅሬታው የቀረበለትን ኮሚቴ ስም እና አድራሻ፣

   ለ) የኮሚቴውን አባላት ስም ዝርዝርና ፊርማ፣

   ሐ) የቅሬታ አቅራቢውን ሙሉ ስምና አድራሻ፣

   መ) እንደአግባብነቱ ቅሬታ የቀረበበት ሰው ስም እና አድራሻ፣

   ሠ) የማስረጃዎች ይዘት እና/ወይም የምስክሮች ቃል በአጭሩ፣

   ረ) የውሳኔ ሀተታና ምክንያት፣

   ሰ) በውሳኔው መሠረት መከናወን ስለሚኖርበት ትእዛዝ እና

   ሸ) ውሳኔው የተሰጠበት ቀንና ሰዓት፡፡

8. እያንዳንዱ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፡-

ሀ) የቀረበን ቅሬታ ከቀረበለት ማስረጃ ጋር በማገናዘብ ይመረምራል፣ ውሳኔውንም በፅሁፍ ያሰፍራል፡፡

ለ) ከቀረበለት ቅሬታ ጋር ግንኙነት ያለው ወይም ያገባኛል ባይ ጥያቄ ሲያቀርብ ከአቤት ባዩ ጋር አብሮ እንዲሰማ እድል ሊሰጥ ይችላል።

ሐ) ቅሬታ ሰሚው ጥያቄ ሲያቀርብ ወይም ኮሚቴው በራሱ አስተያየት ቅሬታ አቅራቢውን እና ቅሬታ የቀረበበትን ወይም ውሳኔ ለመስጠት ይረዳኛል የሚለውን ሰው ጠርቶ ሊጠይቅ ወይም አስፈላጊ ማስረጃ እንዲቀርብለት ሊያደርግ ይችላል፡፡

መ) ቅሬታ ሲቀበል መቼና በስንት ሰዓት እንደሚታይ እና የት እንደሚታይ እንዲሁም ውሳኔ መቼ እንደሚሰጥ ለቅሬታ አቅራቢውና ለሚመለከታቸው ማሳወቅ አለበት።

9. በየደረጃው የሚገኝ ቅሬታ ሰሚ አካል የቀረበለትን ቅሬታ ከተመለከተ በኋላ ውሳኔውን ብቻ ወይንም እንደአስፈላጊነቱ ውሳኔው በአጭሩ ተዘጋጅቶ ቅሬታ ላቀረበው ሰው እና ሌላ ይመለከተዋል ብሎ ያመነው አካል በወቅቱ ማሳወቅ አለበት።

10. ለግልጽነት ይረዳ ዘንድ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የሚሰጠው ውሳኔ በኮሚቴው ጽህፈት ቤት ህዝብ አንዲመለከታቸው በይፋ መቀመጥ አለባቸው፡፡ ሆኖም የሰውን የአካል ወይም የአእምሮ ጤንነት የሚመለከቱ እርምጃዎች በይፋ ላይገለጹ ይችላሉ፡፡

11. የእያንዳንዱ ቅሬታ ውሣኔ በሦስት ቅጂ ተዘጋጅቶ፡-

ሀ) አንዱ ቅጂ ለቅሬታ አቅራቢው ይሰጣል፣

ለ) ሁለተኛው ቅጂ በውሳኔው መሠረት ለሚፈፅም ወይም ቅሬታ የቀረበበትን ውሳኔ ለሰጠው አካል፣

ሐ) ሦስተኛው ቅጂ ቅሬታውን መርምሮ ውሳኔ በሰጠው አካል እጅ በሰነድነት ይያዛል፡፡

**አንቀፅ 26. ማብራሪያ የመስጠት ግዴታ**

በየደረጃው ያለ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ኮሚቴው በሰጠው ውሳኔ ላይ በደረጃ ቀጥሎ ላለው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታ የማቅረብ መብት ላለው ሰው ወይም አካል፡-

1. ቅሬታውን የማቅረብ መብት እንዳለው፣
2. ቅሬታውን ለማን ማቅረብ እንዳለበት፣
3. ቅሬታውን ኮሚቴው ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ማቅረብ እንዳለበት፣ የማስረዳት ኃላፊነት አለበት።

**አንቀፅ 27. ስለ ግልባጭ ይዘት**

ማንኛውም ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የውሳኔ ግልባጭ ለሚፈልግ ቅሬታ አቅራቢ፡-

1. የኮሚቴው አባላት የፈረሙበትን ዝርዝር ውሳኔ አንድ ቅጂ፣
2. ለውሳኔ መነሻ የሆነውን ቅሬታ አንድ ቅጂ የሚሰጥ ይሆናል።

**አንቀፅ 28. ቅሬታ በሁለተኛ ደረጃ የማየት ስልጠን ያለው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፤**

1. በየደረጃው በሚገኙ በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ መሰረት በተቋቋሙ የበታች ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች እንዲታይ የተባለን እና በዚሁ የበታች ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ተመርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ያላገኘ ጉዳይ ሲቀርብለት እና የበታች ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ጉዳዩን የሚያይበት የጊዜ ገደብ ካለበቃ ጉዳዩን መመርመር ሳያስፈልግ ጉዳዩ የት መቅረብ እንዳለበት በመጥቀስ ጉዳዩን ይዘጋል።
2. በየደረጃ ያለው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን ቅሬታ በመመልከት የበታች ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴን ውሳኔ ሊያፀና፣ በከፊል ወይም በሙሉ ሊለውጥ ወይም ሊያሻሽል ይችላሉ።
3. ያስተላለፈውን ውሳኔ በየደረጃው ያሉ የምርጫ አስፈፃሚዎች ተግባራዊ እንዲያደርጉ አስፈላጊውን ትዕዛዝ መስጠት ይችላል።
4. ቅሬታ የቀረበለት ቅሬታ ሰሚ አካል በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት።
5. የአዋጁና የዚህ መመሪያ አስገዳጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቅሬታ የሚቀርበው ለመደበኛ ፍርድ ቤቶች በሚሆንበት ጊዜ አግባብ ያለው የሕግ ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል።

### አንቀፅ 29. ስለ በሁለተኛ ደረጃ የቀረበ ቅሬታ አወሳሰን

በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበ ቅሬታ ላይ በተሰጠ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ቀጥሎ ላለው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ወይም ለቦርዱ የሚቀርብ ቅሬታ ከሆነ እንደሁኔታው በዚህ መመሪያ ስለመጀመሪያ ደረጃ ኣቤቱታ የተመለከቱ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀፅ 30. ስለመተባበር

ማናቸውም የፌዴራልም ሆነ የክልል የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ የፖለቲካ ድርጅት፣ የግል ድርጅት ወይም ግለሰብ ይህንን መመሪያ በሥራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት።

### አንቀፅ 31. የተሻሩ እና ተፈፃሚነት የሌላቸው መመሪያዎች እና አሠራሮች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት የለውም።

### አንቀፅ 32. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በቦርዱ ከፀደቀበት ከየካቲት 4 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**ብርቱካን ሚደቅሳ**

**የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ**